# የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች እና ኢሕአዴግ፤ <u>ከዚኽ ወዴት?</u>

*ከአያል ሰው ደሴ፤- የግል አስተያየት*

***<u>ክፍል አሥራ-አምስት</u>*** *<u>(ከክፍል አሥራ-አራት የቀጠለ)፤-..</u>*

***ኢዴኃኀ.....***

*በአዘጋጅ ኮሚቴው በኩል ከታሰበባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች አንዱ ድርጅቶች ወደዚኽ ጉባዔ እንዲመጡና በመሪዎቻቸው አማካይነት እንዲወከሉ ሲጠየቁ፣ እነሱ በተናጠል ተገኝተው የመሰላቸውን መልእክት አስተላልፈው የሚለያዩበት ወይም "ይኽንን ለመወሰን ውክልና አልተሰጠኝም፣ አማክሬ ልምጣ፣ ወዘተ" በሚል መንገዋለልና ጊዜ ማባከን እንዳይኖር ከወዲኹ የየድርጅቱ አባላት በጉዳዩ ላይ የመምከር ዕድል እንዲኖራቸውና እንዲያገኙ በማድረጉ ላይ ነበር፡፡ ቀደም-ሲል በተሞከሩ የጋራ ሥራ ጥረቶች ላይ ከሚገጥሙት እክሎች አንዱ የሚደረገው ስምምነትና ውል በአብዛኛው የሚደረስበት ፍጥጥም በምክክሩ ላይ በተገኙ ወኪሎችና የአመራር አባላት ላይ ተገድቦ የሚቀርና የየድርጅቱን አባላት በቀጥታ አለማሣተፉ ለጋራው አካል ወይም ለተደረሰበት ስምምነት ቀጣይ-አለመሆን አስተዋፅዖ እንደሚኖረው በጉባዔ አዘጋጅ አካሉ አባላት ዘንድ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ በዚኽ ጉባዔ ላይም ድርጅቶች በጋራ ለመሥራት በመኻላቸው እንዲፈጠጥሩት የታለመው በጋራ ራዕይ ላይ የተመሠረተ የጋራ የትግል አቀናባሪ አካል (መድረክ ወይም ኅብረት) በየድርጅቱ አመራር ላይ ባሉ ብቻ ተንጠልጥሎ እንዳይቀርና የሚፈጠረው የጋራ አካል ከላይ-እስከ-ታች ባሉ የየድርጅቱ አባላት ዘንድ የጠራ ግንዛቤ የተወሰደበትና "የኔ ነው" ስሜትን የተላበሰ አመኔታን እንዲያተርፍና ሙሉ ድጋፍን ያገኘ እንዲሆን አስፈላጊነቱ ግልጥ ነበር፡፡ ስለሆነም አዘጋጅ ኮሚቴው የድርጅቶች ተወካዮች ወደ ጉባዔው ከመምጣታቸው በፊት በየድርጅታቸው አባሎቻቸው ስለ ስብሰቡና ዓላማው በግልጥ የመከሩበት እንዲሆን ፍላጎት ነበረው፡፡ ለዚኽም ምሑራንን በቀጥታ በማሣተፍ በኮሚቴው ተዘጋጅቶ የጋራ ግንዛቤ-አስጨባጭ፣ የአብሮ-መቆሚያ፣ የጋራ መሥሪያና መግባቢያ እንዲሆን ታስቦ ለድርጅቶች እንዲደርስ በተደረገው የራዕይ ሰነድ ላይ የየድርጅቱ አባላት አስቀድመው የተቻለውን ያኽል ምክክር እንዲያደርጉበትና በተለይ በአንድ የጋራ መዋቅር ሥር የመሥራት አስፈላጊነትን በትክክል ባገናዘበና በታመነበት መልኩ ተግባራዊ መሆን እንዲችል ተወካዮች ሙሉ ውሳኔ ለማደረግ ግልጥ ኃላፊነት የተሰጣቸው እንዲሆኑ በተለያዩ መልኮች መልዕክቱን ለማስተላለፍ ተሞክሯል፡፡ ጉባዔው ከመደረጉ በፊት አስቀድሞ ከተላለፈው የራዕይ ሰንድ በተጨማሪ በአንዳንድ ድርጅቶች (ከኅብረሕዝብ፣ ከመኢሶን እንዲሁም ከመኢኣድ፣ ደቡብ ኅብረትና ኦብኮ በጋራ) የቀረቡ ጥናቶች ለተሣታፊ ድርጅቶች እንዲደርሱ ተደኅል፡፡ በኋላም በኢዴፓ በኩል ድርጅቱ በልዩ ልዩ የአገሪቱ ጉዳዮች ላይ ያለውን አመለካከትና እምነት የሚዳስስ የዳሰሰ ሰነድ ለተሣታፊ ድርጅቶች ታድሏል፡፡*

*ጉባዔው መቸ እና የት መደረግ እንደሚኖርበት አማራጮች (አፍሪቃ፣ አውሮጳ እና አሜሪካ) ቀርበው ሠፊ ውይይት፣ ምክክርና የአሣብ ልውውጥ ተደርጎባቸዋል፡፡ በመጨረሻም የጉባዔው ጊዜ ትምሕርት ቤቶች በሚዘጉበትና ብዙዎችም ከሥራ ገበታዎቻቸው እረፍት መውሰድ በሚችሉበት በአገራችን ክረምት በውጭው (በምዕራቡ) ደግሞ በጋ ወራት (በሐምሌ ወር መጨረሻና በነሐሴ መጀመሪያ ላይ)፣ ቦታውም በአሜሪካ ዋና ከተማ (ዋሽንግተን ዲ.ሲ. አካባቢ) እንዲሆን ተወሰነ፡፡*

*ጉባዔ አዘጋጅ አካሉ በታቀደው የድርጅቶች አገር-አቀፍ ታላቅ ስብሰባ ላይ መገኘትና መሣተፍ የሚችሉና የሚኖርባቸው ድርጅቶች ጉባዔው ይዞት እንዲወጣ ከታለመለት እቅድና ከሚጠበቅበት ውጤት አኳያ እንዲታይ ማድረጉ ላይ ተመካክሮ ውሳኔ አድርጓል፡፡ አዘጋጅ ኮሚቴው ሁሉም ድርጅት በጉባዔው ላይ ተሣታፊ እንዲሆን ያላደረገው ጥረት አልነበረም፡፡ የጉባዔው መጠራት አይቀሬ እየሆነና ቀኑም እየተቃረበ ሲሄድ ብዙ ድርጅቶች ተሣታፊ ለመሆን ጥያቄዎች ከየ-አቅጣጫው ማቅረብ ጀምረው ነበር፡፡ የፖለቲካ ድርጅት*

*የተባለ ሁሉ በጉባዔው ላይ ለመሣተፍ ጥያቄ ያላቀረበ አንድም አልነበረም፡፡ ሆኖም አዘጋጅ አካሉ እንደ-ጠበቀው ሁሉ ጥያቄውን ካቀረቡት መኻል አንዳንዶቹ ቀደም-ሲል የሚታወቁም ሆነ ስለ-ኅልውናቸው ተጨባጭ ማረጋገጫ የተገኘላቸው አልነበሩም፡፡ የሆነ-ሆነ በአዘጋጅ ኮሚቴው በኩል ይኽ ሁኔታ ሊፈጠርና አስፈላጊው ጥንቃቄ ካልተደረገ ጉባዔው በተለይ በአገዛዙና በመሰሎቹ ሊሰረጅና እክል ሊገጥመው እንደሚችል ስጋት ስለ-ነበር፤ በአንድ በኩል ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ የሚያችል፣ በሌላ በኩል ግን በአጉል ጥርጣሬ ላይ በተመሠረተ አመለካከት ፍትኀ-ኅደል ውሳኔ እንዳይደረግና ተሣታፊ መሆን የሚችሉና የሚገባቸው ድርጅቶች ያለ-አግባብ የመሣተፍ መብታቸው እንዳይጣስ ማድረጉ አግባብነት ስላለው በሁሉም ድርጅቶች ላይ ያለ-ምንም አድልዖ እኩል የሚሠራ ባለ ስምንት ነጥብ መመዘኛ እንዲወጣ ተደረገ፡፡ (APC, Criteria.pdf) እያንዳንዱ በጉባዔው ተሣታፊ ለመሆን ጥያቄ ያቀረበ ድርጅትም እያንዳንዱን የመመዘኛ ነጥብ ማሟላት አለ-ማሟላቱ በዝርዝር እየታዬና ውይይትና ክርክር እየተደረገበት ኮሚቴው የመጨረሻ ውሳኔውን በሰኔ ወር መጨረሻ ዘጠና አምስት ዓ/ም ላይ በማስተላለፍ ለእያንዳንዱ ጥያቄ-አቅራቢ ድርጅት ምላሹን ለመስጠት ሞክሯል፡፡ ኦነግ በመጨረሻው ሰዓት በጉባዔው ላይ በታዛቢነት ለመገኘት ጠይቆ ኮሚቴው ጥያቄውን ወዲያውኑ ውድቅ አድርጎታል፡፡*

*እንደተጠበቀው በአገዛዙ በኩል ጉባዔውን ለማክሸፍ ተቃዋሚ-መሣይ የበግ ለምድ-ለባሽ የተኩላ ባኅታውያንን ሣይቀር በመጠቀም የተቀናበረ ዘመቻ ማድረጉና መራወጡ አልቀረም፡፡ የሚያሣዝነው ግን ቅን-አሣቢ ሆኖም በፖለቲካው ዘላቂ አካሄድ ላይ የረቀቀ ግንዛቤ ጉድለት ጥንውት የኅበኛቸው ወገኖችም "የሞኝ አጋፋሪ" በመሆን የተወሰኑ ድርጅቶች ብቻ ከኦነግ ጋር "ግንባር" እንዲፈጥሩ ገንዘባቸውን ሲከሰክሱና ጊዚያቸውን ሲያባክኑ ማየቱ እና ያ እርምጃም የጉባዔውን ዝግጅት አደናቃፊ ወደ-መሆኑ ደረጃ ያቀና መሆኑ ነበር፡፡ ሆኖም በጉባዔ አዘጋጅ አካሉ በኩል ሁሉንም እንዳመጣጡ በማስተናገድ ብቻ ሣይቆጠብ ዋና ንጥጥሩንና ትኩረቱን ከዝግጅቱ ላይ ሣያነሳ ድርጅቶች ከመሥመር እንዳይወጡና በስብሰባው ላይ መሣተፍ ያለባቸው ክፍሎች እንዳይቀሩ ጠንካራ ስልታዊ ግፊቱን አጠናክሮ በመቀጠሉ፣ ጉባዔውን ለማደናቀፍ የተሸረቡትን ተንኮሎችና የተደነቀሩትን እንቅፋቶች በቀላሉ ማክሸፍ ተችሏል፡፡*

*ከአገር-ውስጥና ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች የመጡ ተወካዮችም ቅድመ-ጉባዔ መተዋወቅ እንዲያደርጉና እንዲመካከሩም ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ተደርጓል፡፡ ስብሰባዎች በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ እንዲከናዎኑ ለማገዝ፣ በአንዳንድ ክፍሎች በኩል የተወሰኑ ድርጅቶችን ከስብስቡ ነጥሎ ለማውጣት ለነበረው አጉል ሙከራም ዕድል ላለመስጠት፣ ልዑካንም ከመደበኛ የስብሰባ ሰዓት ውጭ በደንብ የመተዋወቅ ዕድል እንዲኖራቸው፣ የጎንዮች ምክክር ማድረግ እንዲችሉና ሙሉ ትኩረታቸውንና ጊዚያቸውን በመጡበት አገራዊና ሕዝባዊ ዋነኛ ጉዳይ ላይ እንዲያደርጉ በማሰብ የሁሉም ድርጅቶች የልዑካን ቡድን ጉባዔው ከሚጀመርበት ዋዜማ (ሐምሌ አሥራ-ስምንት ቀን ዘጠና-አምስት ዓ/ም) ጀምሮ እስከሚጠናቀቅበት ዕለት ድረስ ከሰባት ቀኖች በላይ ጉባዔው በሚካሄድበት ሆቴል ውስጥ (ሮክ ቪል ሜሪላንድ በሚገኘው ደብል-ትሪ ሆቴል) እንዲያርፉ እና ቁርስ፣ ምሳና እራት እዚያው እንዲሆን ተደረገ፡፡ (ማረፊያን የመሣሰሉ መስተንግዶዎች ለአንዳንድ ከአሜሪካ ውጭ ለመጡ የልዑካን ቡድኖች ከዚያም ቀደም-ሲል ጀምሮ ተሰጥቷል)፡፡*

*ታዋቂ ግለ-ሰቦች እና ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) እስከ የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር (ኢመማ)፣ ከኢትዮጵያ አገራዊ ጉባዔ (ኢአጉ) እስከ ነፃ ጋዜጠኞች ማኅበር፣ ከሴቶች እስከ ወጣቶች ማኅበራት፣ ወዘተ. ያሉ የሲቪክና የሙያ ማኅበራት ተወካዮች ስብስቡ የታሰበውን አዎንታዊ ውጤት ይዞ እንዲወጣ በአካል በመገኘት ምክሮቻቸውን እንዲለግሱና ያሏቸውን አስተያየቶች እንዲያስተላልፉ በአዘጋጅ ኮሚቴው አማካይነት ጥሪ ተደርጎላቸዋል፡፡ ለአንዳንዶቹም ወጭአቸው እንዲሸፈንላቸው ጥረት ተደርጓል፡፡ በጉባዔው ላይ በሁሉም አቅጣጫ የተሰለፉ ኃይሎች አስፈላጊው ተሣትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ በአዘጋጅ ኮሚቴው በኩል ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡*

*ለ) የጉባዔ አካሄድና አከዋዎን፤- እያንዳንዱ ድርጅት በጉባዔው ላይ በሦስት፣ ሦስት የአመራር አባላቱ እንዲወከል በተወሰነው መሠረት ለመሣተፍ ፍላጎትና ዝግጁነት ካሣዩት*

አሥራ-ሰባት ድርጅቶች ውስጥ አሥራ-አምስቱ ወኪሎቻቸውን መላክ ችለዋል፡፡ (የአፋር ዴሞክራሲያዊ አንድነት ድርጅት ከልዑካን ቡድኑ መኻል ሁለቱ ከአፍሪቃ ቪዛ በጊዜው ማግኘት ባለቻላቸው የተሣተፈው በአንድ አባል ብቻ ነበር)፡፡ (APC, Participating Orgs and Deligates.pdf)

ጉባዔው ስብሰባውን ከመጀመሩ አንድ ቀን አስቀድሞ ቅዳሜ ሐምሌ አሥራ-ዘጠኝ ቀን (July 26, 2003) ከቅርብና ከሩቅ ጥሪ የተደረገላቸው የሐይማኖት አባቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ የክብር እንግዶች፣ የማኅበረሰብ መሪዎች፣ ልዩ ልዩ የኅብረተሰባችን ተጠሪዎች፣ የሙያ ድርጅቶችና ስብስቦች ተወካዮች፣ ወዘተ.. በተገኙበት ልዩ የመክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ተደርጓል፡፡ ይኸ ታሪካዊ ዝግጅት በሐይማኖት አባቶች ቡራኬ ተከፍቷል፡፡ (የአክብሮት ጥሪው ለሁሉም የሐይማኖት ተቋሞች የተላለፈ ሲሆን ጥሪውን በመቀበል በቦታው በመገኘት ታላቅ አባታዊና እጅግ የረቀቀ መልዕክት ያስተላለፉት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያንን በመወከል የተገኙት ብፁዕ አቡነ ኤልያስ ነበሩ፡፡) ከቡራኬው ቀጥሎ በመክፈቻው ሥነ-ሥርዓት ላይ የተገኙትን እንግዶችና የድርጅቶችን ተወካዮች እንኳን ደኅና መጣችሁ በማለትና አዘጋጅ አካሉ ጉባዔውን እንዴት እንደሚመለከተው፣ ከተሰባሰቡት የፖለቲካ ድርጅቶችና ከመሪዎቻቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን እንደሚጠብቅ፣ ወዘተ.. በማሣሰብ በዝግጅት ኮሚቴው ሰብሳቢ ንግግር ተደረገ፡፡ (APC, Opening, Address by Committee Chairman, July 26, 2003.pdf). በመቀጠልም ከምትክ-የለሹ አንጋፋ የኪነት ሰው ከሎሬት ፀጋዬ ገብረ-መድኅን ጀምሮ ታዋቂ ኢትዮጵያውያን የአደራ መልዕክቶቻቸውን፣ ከልዩ ልዩ የሲቪክና የሙያ ድርጅቶች ተወካዮች እንዲሁም ከበርካታ አካባቢዎች የመልካም ምኞት መልዕክቶች ተላለፉ፡፡
የአዘጋጅ አካሉ ሰብሳቢ እያንዳንዱን የድርጅት የልዑክ ቡድን በማስተዋወቅ የየልዑኩ መሪ በእንግዶች ፊት ለጉባዔው መሣካት ያለውን ዝግጁነት እንዲገልጥ ዕድል ተሰጠ፡፡ በመቀጠል ለተጋባዥ እንግዶች፣ ለልዑካን ቡድኖች እና ጥሪ ለተደረገላቸው የውጭ-አገር ዜጎች (የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የኮንግረስ ተወካዮችና ሌሎችም) በተገኙበት የትውውቅና የጭውውት ግብዣ (cocktail) ተደረገ፡፡

በማግሥቱ እሁድ ሐምሌ ሃያ ቀን ዘጠና-አምስት ዓ/ም ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ጀምሮ ለሰባት ቀናት የዘለቀው ጉባዔ በሰብሳቢው ከፋችነትና በልጅ ሚካኤል እምሩ ጥልቅ መልዕክት ያዘለ ንግግር እንዲጀምር ተደረገ፡፡ በጉባዔው የመጀመሪያ ቀን ላይ አርባ-ሁለት የየድርጅቱ ተወካዮች (አርባ-አንድ ወንዶችና አንዲት ሴት) እና ዘጠኝ የአዘጋጅ ኮሚቴው አባላት በድምሩ አምሣ-አንድ ተሣታፊዎች፣ ሦስት ቃለ-ጉባዔ ያዥዎች፣ ሁለት የጉባዔውን ሂደት በመቅርፀ-ድምፅ (ቴፕ) እና በተንቀሣቃሽ-ጠንቃሪ (ቪዲዮ) ዘጋቢዎች፣ ሁለት አጠቃላይ እገዛ አድራጊዎች በአዳራሹ ውስጥ የነበሩ ሲሆን፣ በውጭ በኩል ፀጥታ የሚያስከብሩ ከየድርጅቱ የተመደቡ አባላት ነበሩ፡፡ እያንዳንዱ የልዑክ ቡድን አባል እራሱን በማስተዋወቅና በቡድን መሪው አማካይነትም ድርጅቱ ያለውን አቋም ጠቅለል ባለ ሁኔታ እንዲገልጥ ተደረገ፡፡ ቅድሚያ በሦስት አንቀፆች የተጠቃለሉ አሥራ-ሦስት ነጥቦችን የያዘ የስብሰባ አካሄድ ሥነ-ሥርዓት ደንብ እንዲፀድቅ በማድረግ የጉባዔውን የየቀን ስብሰባዎች በኃላፊነት የሚመሩ ሊቃነ-መናብርትና ፀሐፊዎች በርጫ እንዲሰየሙ ተደረገ፡፡ በመቀጠልም የጉባዔውን ሂደት በመቅረፀ-ድምፅ (ቴፕ) እና በተንቀሣቃሽ-ጠንቃሪ ወይም በትዕይንተ-ልቃቂት (ቪዲዮ) ከመዘገብ በተጨማሪ ቃለ-ጉባዔ የሚይዙ ሰዎችን በመመደብ፣ በአዘጋጅ ኮሚቴው ፀሐፊ (አቶ ፋሲካ በለጠ) አጭር ዘገባ ከቀረበ በኋላ ሰብሳቢው (አያል ሰው ደሴ) ጉባዔውን እንዲመሩ ለተመረጡት መድረኩን አስረከቡ፡፡ በጉባዔው ሂደት አንዳንድ ነጥቦች ላይ ጥያቄ ቢነሣ መልስና ማብራሪያ ለመስጠትና ሂደቱ እክል እንዳይገጥመው የሚቻለውን እገዛ ማድረግ እንዲችል በማሰብ የዝግጅት ኮሚቴው አባላት በዚኸ ጉባዔ ላይ የየድርጅታቸው የልዑክ ቡድን አባል በመሆን ፋንታ ኮሚቴው ሳይበተን እንደ አንድ አካል እንዲገኝ የቀረበውን ጥያቄ ቤቱ ተቀብሎ አፀደቀው፡፡ ይኸ እንዲሆን የኮሚቴው አባላት የፈለጉበት ተጨማሪ ምክንያት ግን ጉባዔው የታሰበውን ውጤት ይዞ እንዲወጣ ድርጅቶች ከጋራው ጥረት እንዳያፈነግጡ በየድርጅቶቻቸው የሚጫወቱትን ሚና ለመቀጠል ነበር፡፡ ሆኖም የአዘጋጅ አካሉ አባላት በዝምታ ከመታዘብና ጥያቄ ሲነሣ አስፈላጊ ማብራሪያ

ከመስጠትና አጠቃላይ የክርክር ነጥቦች ላይ አሣባቸውን ከመስጠት ውጭ ድምፅ አይሰጡም።

የጉባዔው ዋና-ዋና የመወያያ (የአጀንዳ) ነጥቦች (ርዕሰ-ጉዳዮች)፤ የአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታና መሠረታዊ ችግሮቻችን፣ ቀደም-ሲል የተደረጉ የጋራ ጥረቶች አስተዋፅዖ፣ ጉድለትና ድክመት፣ የጋራ ራዕያችን ምንድን ነው? ምን መደረግ አለበት? እና የትግል ስልትና የጋራ መዋቅር የሚሉት ነበሩ።

ሐምሌ ሃያ የተካሄደው የመጀመሪያው ቀን ስብሰባ ሙሉ ትኩረት የአገሪቱን አጠቃላይ ሁኔታ በመገምገሙ ላይ ሲሆን፣ አስቀድሞ በተዘጋጀው ሰነድ ላይ ተጀምሮ ሰፊ ውይይት ተደርጎበታል። የመሠረታዊ ችግሮቹ መንስዔዎችና ምክንያቶችም በዝርዝር ታይተዋል። አጠቃላይ የጋራ ግንዛቤ ነጥቦች ሲዘረዘሩ፣ (APC, Common Understanding and Objectives.pdf) በአጭሩ አገሪቱ የምትገኝበት ሁኔታ "አሣዛኝ፣ አሣፋሪና ዘግናኝ" እንደሆነ የጉባዔው አጠቃላይ ግንዛቤ ሆኖ ተወሰደ። በሁለተኛው ቀን (ሐምሌ ሃያ-አንድ) በዋለው ስብሰባ ላይ ጉባዔው በጥሞናና በዝርዝር የተመለከተው "የኅብረት ጥረቶች፣ ጥንካሬዎች፣ ችግሮችና ድክመቶች" በሚል ርዕስ የቀረበውን ቀደም-ሲል የተመሠረቱ የጋራ የትግል መድረኮች፣ የተደረጉ የኅብረት ምሥረታ ጥረቶችንና የትግል ሂደቶችን በተመለከተ ነበር። በዚኽ ጉዳይ ላይ ከጉባዔ ተሣታፊዎች ከመቶ-አሥራ-አራት በላይ የአስተያየት ነጥቦች ቀርበዋል። እነኝኽ ሠፊ አስተያየቶች ሁሉም በሚስማማባቸው በአምስት አዎንታዊ ገፅታዎችና ሃያ-አምስት አሉታዊ፣ የድክመትና የግድፈት ነጥቦች ተጨምቀው ለቤቱ በንባብ ከተደመጡ በኋላ የጉባዔው ግንዛቤ ሆነው ተወሰዱ።

በሦስተኛው ቀን (ሐምሌ ሃያ-ሁለት) በተደረገው ስብሰባ ላይ የውይይቱ ዓይነታ ነጥብ የጋራ ራዕይን በተመለከተ ነበር። ለመግባቢያና የጋራ መሥሪያ እንዲሆን ከተዘጋጀው የራዕይ ሰነድ አኳያ እያንዳንዱ ድርጅት ያለውን ራዕይ በአጭር-በአጭሩ እንዲገልጥ ዕድል ከተሰጠ በኋላ ድርጅቶች በተናጠል ከያዙአቸው ውስጥ ሁሉንም ሊያስተሣሥር የሚችልና በጋራ የሚታገሉለት የጋራ ራዕይ ማጠናቀር አስፈላጊ በመሆኑ የሚደረገው ትግል በአገሪቱ መንግሥት ለመለወጥ ብቻ ሣይሆን የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት መሆን እንዳለበት፣ ዜጎች 'አንድ-ሰው-አንድ-ድምፅ' በሚለው መርኅ ነፃና-ርቱዓዊ ምርጫ በማድረግ ሁለንተናዊ መብቶቻቸውን የሚያስከብሩበት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለቤት እንዲሆኑና አገራቸው ኢትዮጵያ የአምባ-ገነን ሥርዓት አዙሪት አክትሞ፣ ረሃብና አንገት-አስደፊ ችግር፣ መሃይምነትና ኋላ-ቀርነት፣ በሽታና የሰላም እጦት ተወግደው፣ የዜጎች እኩልነት የተረጋገጡባትና የፍትኅ አገር እንድትሆን ማስቻል የሁሉም የጋራ ራዕይ ሆኖ ተወሰደ።

በቀጣይ ቀኖች በተደረጉ ስብሰባዎች ላይ ጉባዔው 'አስቸኳይ የተባበረ ምላሽ' እንደሚያስፈልገውና 'አሳዛኝ፣ አሳፋሪና ዘግናኝ' ብሎ ለፈረጀው የአገሪቱ ሁኔታ አግባብነት ያለው መፍትኄ ላይ ያተኮሩ ውይይቶች ተደርገዋል። ውይይቶቹና ክርክሮቹም አንደኛ ድርጅቶች በሚያደርጉት የተናጠል ትግል የሚፈልጉትን ሕዝብንና አገርን የሚጠቅም ውጤት ማምጣት ስለማይችሉ ከአሁን በኋላ ጥረታቸውን በአንድ የጋራ መታገያ ድርጅት ሥር አስተባብረው የጋራ ትግል እንዲያደርጉ፤ ሁለተኛ ይኽ በአገር-ውስጥም ሆነ ከአገር-ውጭ ያሉ ድርጅቶችን ያቀፈ ድርጅት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) እንዲሆን፣ ሦስተኛ ከዚያ በፊት የነበሩ የጋራ የትግል መድረኮች (ኅብረቶች) ከዚያን ቀን ጀምሮ ኅልውናቸው እንዳከተመ (ለጊዜው ከአማራጭ ኃይሎች በስተቀር*)፤ አራተኛ የጋራ ኃይሉ የትግል ስልት ሰላማዊ እንደሆነ፣ አምስተኛ ድርጅቱ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ የሚደረገውን ሕዝባዊና ሰላማዊ ትግል በተጠናከረ መልክ እያጠናከረና ዓለም-አቀፍ ድጋፍም እንዲገኝ ጥረት በማድረግ ገዥው ፓርቲና መንግሥት በአገራችን ነፃ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ፍትኃዊና ርቱዓዊ ምርጫ እንዲያደርግ ማስገደድ፣ ወዘተ የሚሉ ውሳኔዎችን ሲወስን፤ ይኽንን በተግባር የሚተርጉም አደረጃጀትና አወቃቀር መሥርቷል።

(* ይኽ ውሳኔ አማራጭ ኃይሉን ለጊዜው አይመለከተውም የተባለበት ምክንያት በወቅቱ በአማራጭ-ኃይሎች ስም በሕዝብ መስዋዕትነት ተመርጠው ፓርላማ ውስጥ ያሉ ተመራጮች ስለ-ነበሩ አማራጭ ኃይሉ እንደሌለ ወይም እንዳከተመ መወሰን መስዋዕትነት የተከፈለበትን የሕዝብ ግምፅ መሻር ስለሚሆን እስከ ቀጣዩ ምርጫ - ዘጠና-ሰባት ድረስ ማቆየቱ አግባብነት ስለነበረው ነው።)

***በክፍል አሥራ-ስድስት ይቀጥላል.....***